የ 5 ኛ ክፍል ማስታወሻ
ምዕራፍ አስር
ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ
10.1. የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ምንነት
✡.ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አንድ ሰው በተነሳሽነት ከሌሎች ጋር በጋራ የሚያከናውነው ተጨባጭ ተግባር ነው፡፡
*.በት/ቤት በሚከናወኑ ሥራዎች ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማድረግ ከማንኛውም ትጉህ ተማሪ የሚጠበቅ ነው፡፡ይህንን ማድረግ ተጨማሪ ልምድና እውቀት ለማግኘት ከውጤቱም ለመጠቀም ያስችላል፡፡
#.ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የጋራ እንቅስቃሴ ይሻል፡፡ገንዘብን፡ጉልበትንና እውቀትን አዋህዶ በጋራ መሥራት በላቀ ሁኔታ ውጤታማ ያደርጋል፡፡
10.2 የንቁ ሕዝባዊተሳትፎ አስፈላጊነት
*.በት/ቤት የንቁ ተሳትፎ ጥቅም;-
•.ጉልበተኛ ጥቃት አይደርስባቸውም፡፡
•.ጥሩ የሆነ የትምህርት ሥርአት ይሰፍንላቸዋል፡፡
•.ጤና የማይጎዳና መንፈስን የሚያረካ መማሪያ ክፍል ይኖራቸዋል፡፡
•.እንዲሁም ትምህርትን በጥሞና ለመከታተል የሚያስችል ተስማሚ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡
10.3 የሕዝባዊ ተሳትፎ ዓይነቶች
;-ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ በሁለት ይከፈላል:
1.በት/ቤት የሚካሄድ
2.በመኖሪያ/በስራ ቦታ/ የሚካሄድ ሕዝባዊ ተሳትፎ ነው፡፡
10.4 የሲቪክ ማህበራት
✡.የሲቪክ ማሕበራት ማለት የንግድ ያልሆነ፡ ከፖለቲካና ከመንግሥት ነፃ የሆነ ድርጅት ማለት ነው፡፡ በጋራ ለመሥራት ከሚደራጁት አካላት መካከል የሲቪክ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ተቋማት የሚካሄድ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ለዴሞክራሲ ማደግ፡ ለሰላም መረጋገጥና ለልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
የሲቪክ ማህበራት ባሕርያት;-
•.የፖለቲካ ወገንተኝነት የሌለው
•.በመንግሥት የማይመራ(ከመንግሥት ነፃ የሆነ)
•.በአባላቱ በጎ ፈቃድ የሚንቀሳቀስ
•.ለአትራፊነት ያልተደራጀ

•.ገቢውን ከአባላቱ መዋጮና ከለጋሾች የሚያገኝ፡፡

ዕራፍ አስራ አንድ
ዕውቀትን መሻት
11.1 የዕውቀት ምንነት ጥቅም
✡. ዕውቀት;- ነገሮችንና ሁኔታዎች በብቃት ለመረዳት የሚያስችል ብቃት ነው፡፡
*.ዕውቀት አካባቢንና ዓለምን የመረዳት ሂደት ነው፡፡ሰው አካባቢውን በመመልከት አስተሳሰብን ያሰፋል፡፡
*.ዕውቀት ከተለያዩ ተፅዕኖዎች ነጻ እንድንሆን የሚያግዘን መሣሪያ ነው፡፡
ለምሳሌ;- የኮሮና ቫይረስ በሽታ እንዳያጠቃን የሚያደርጉ ነገሮችንም በዕውቀት እንደርስባቸዋለን፡፡ ስናውቃቸውም እንዳያጠቁን የሚያስችል የመከላከያ ዘዴ እንቀይሳለን፡ ካጠቁንም ለመዳን የሚያስችል መድኃኒት እንድናገኝ ዕውቀት በጣም ያስፈልገናል፡፡
ስለዚህ ዕውቀት እየተሻሻለ በሄደ ቁጥር ኑሮም በጣም ይሻሻላል፡፡
✡.እናንተም በት/ቤት የተሻለ ዕውቀት በገበያችሁ ቁጥር የበለጠ ጎበዝና ተመራማሪ ተማሪዎች ትሆናላቹ፡
11.2 መረጃ የሚገኝባቸው ዘዴዎች
*.መረጃ ስለጉዳዩች ለማወቅ የሚሰበሰብ ጥሬ ሐሳብ ነው፡፡
✡.መረጃ በጽሁፍ፡ በሬዲዮ፡ በቴሌቪዥንና በመሳሰሉት ዘዴዎች ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የግንዛቤ ወይም የዕውቀት ምንጭ ነው፡፡ #.መረጃዎችን በማየት፡ በማዳመጥ፡ በማሽተት፡ በመዳሰስ፡ ወይም በመቅመስ ልናገኛቸው እንችላለን፡፡ መረጃዎችን ከአካባቢያችን ወይም ከአካባቢያችን ውጪ ልናገኝ እንችላለን፡፡
*.ከአካባቢያችን ከምናገኛቸው መረጃዎች መካከል የአካባቢ ሠላም፡ የመምህራን ጾታና ዕድሜ ተዘውትረው የሚከበሩ በዓላት ሲሆኑ *.ከአካባቢያችን ውጪ የምናገኛቸው ደግሞ የሕዝብ ተወካዮች ምርጫ ውጤት፡ የዓለም የነዳጅ ዋጋ ሁኔታ፡ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት ናቸው፡፡
*.ት/ቤቶች ከሁሉም የበለጠ የዕውቀት ማግኛ ቦታ ነው፡፡ በልዩ ልዩ ሙያዎች የሰለጠኑ ምሁራን በት/ቤት ይገኛሉ፡፡ እነሱም እኛን ለመርዳት ቀን ከሌሊት ይደክማሉ፡፡
*.በጉብኝት ስለመሬት አቀማመጥ፡ ስለ አየር ሁኔታ፡ ስለሕዝቦች ባሕል ዕውቀት እንቀስማለን፡፡
✡.ታዲያ እነዚህን ከተለያዩ ምንጮች ያገኘናቸውን መረጃዎች በሚገባ ለመረዳትና ከራሳችን ጋር ለማዋሀድ በተግባር ላይ ማዋል አለብን፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን፡ ጥቅምና ጉዳታቸውን እያስተዋልን፡ ደጋግመን ማጥናት ይኖርብናል፡፡
✡.በዚህም ውጤታማ ለመሆን በማስታወሻ መመዝገብ ወይም በካሴት መቅረጽ ይጠበቅብናል፡፡
11.3 ኃላቀር አስተሳሰብና አመለካከት
✡.ኃላቀር አስተሳሰብ በትምህርት ያልተደገፈ፡ በጭፍን የሚታመን ወይም በልማድ ላይ ብቻ የተመሰረተ ጎታች አመለካከት ነው፡፡

#.በኃላቀር አመለካከት ከተመራን ለምናደርገው ነገር ሆነ ለምናከናውነው ተግባር አሳማኝ ምክንያት የለንም:: #.በማይጨበጡ ግምቶችና እምነቶች እንድንገዛ ይገፋፋናል፡፡ ለምሳሌ;- "ሴት ብታውቅ ወንድ ያልቅ"; "ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም"; "ወንድ ባለ በዕለት ሴት ባለ በዐመት"; እንዲሁም "የሰው ቡዳ አለ" ብሎ ማመን ወነኞቹ የኃላቀር አመለካከቶች መገለጫ ናቸው፡፡
✡.ኃላቀር አመለካከት ያለው ሕዝብ ዕድገቱ አይፋጠንም፡፡ ም/ክ ጠቀሜታ ያላቸው ነገሮች እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡ ጎጂ የሆኑት ግን ይበረታታሉ፡፡ ይህ ደግሞ ዕውቀት እንዳይስፋፋ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ አዲሱ ትውልድ ኃላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ሊያስወግዳቸው ይገባል፡፡
11.4 የንባብ ባሕል
✡.ንባብ በወረቀት ወይም በሌላ ዝርግ አካል ላይ በሆሔያት ተጽፎ የቀረበን ሐሳብ መቅሰሚያ መንገድ ነው፡፡ከጨቅላ ዕድሜያችን ጀምረን እንድንጎብዝ መጻህፍትን አዘውትረን ማንበብ ይኖርብናል፡፡ በንባብ አማካኝነት ዕውቀታቸውን አዳብረው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች አሉ፡፡
ለምሳሌ;-በሀገራችን እንደነ ከበደ ሚካኤለ፡ ይልማ ዴሬሳ፡ ጸጋዬ ገብረመድህንና ሌሎችም ግለሰቦች "ታላላቅ ሰዎች" መሆን የቻሉት ገና ከልጅነታቸው ጀምረው የንባብ ልምድ ስለነበራቸው ነው፡፡
11.5 የትምህርት አጠናን ዘዴ
✡.ጥናት;-ዕውቀትን በሚገባ ለመጨበጥ ጽሑፋዊ ወይም ሌሎች የመረጃ ፍንጮችን የመፈተሽ ዘዴ ነው፡፡
#.ዋና ዋና የትምህርት አጠናን ዘዴ;-
1.ቅድመ ጥናት፡ አመቺ የጥናት ጊዜ፡ ቦታ የጥናት ቁሳቁሶችን መምረጥ፡ የጥናት ዕቅድ መንደፍ፡፡
2.ዐውደ ጥናት፡ በተመስጦኦ ማንበብ፡ ከራስ ተሞክሮና በአካባቢ ካለ ዕውነታ ጋር ማገናዘብ፡ ማስታወሻ ፣መያዝ፡፡ 3.ድኃረ ጥናት፡ የያዙትን ማስታወሻ መከለስ፡ የተገኘው ዕውቀት በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥራ መሥራት ፡፡ #------------#